## የተልእኮ ትምህርት ስድስት

## የኦሪት ዘጸአት ጥናት

- **ከሙሴ ዘመን በፊት ከአብርሃም ጊዜ ጀምሮ ዐሥራት መክፈል የተለመደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ ለመሆኑ ዐሥራት ማለት ምን ማለት ነው? አጀማመሩስ እንዴት ነው?**

ዐሥራት ማለት አንድ ዐሥረኛ ማለት ነው። ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ከማንኛውም ገቢ ዐሥረኛው እጅ ለሃይማኖት መሪዎች ወይም ለመንግሥት ይሰጥ ነበር። ነገር ግን እንዴት እንደተጀመረ አይታወቅም። ከሙሴ ዘመን በፊትና እንዲሁም ከባቢሎን እስከ ሮም ድረስ ይሠራበት ነበር። አብርሃም ለመልከ ጼዴቅ ዐሥራትን ሰጠው (ዘፍ. 14፡20)። ያዕቆብም ለእግዚአብሔር ዐሥራትን ለመክፈል ተሳለ(ዘፍ. 28፡22)። ሌዋውያን ካህናት እንዲጠቀሙበት(ዘኍ 18፡21-32)፣ ምድር ከምታፈራውና ከከብትም ወገን ዐሥራት እንዲሰጥ ታዘዘ (ዘሌ 27፡30-33)። የሚከፈልበት ጊዜ ተወሰነ (ዘዳ. 12፡5-18፤ 14፡22-29)። ዐሥራትም ሲከፍሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይባርካል(ዘዳ 26፡13-15፤ ሚል 3፡10)። ፈሪሳውያን ከቅመማ ቅመም ሳይቀር ዐሥራት ይከፍሉ ነበር(ማቴ 23፡23)። ሐዋርያት ስለ ዐሥራት አልጻፉም፤ ሆኖም እንደ እግዚአብሔር በረከት መጠን በልግስና በውዴታ ዐሥራት መስጠት ይገባል(1ቆሮ 16፡1-4፤ 2ቆሮ 9፡6-12)።

- **እስራኤላውያን በሙሴ መሪነት ከግብጽ ባርነት ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ ፋሲካ መከበር እንደተጀመረ ይነገራል፤ ለመሆኑ ፋሲካ ማለት ምን ማለት ነው? አጀማመሩስ እንዴት ነው?**

ፋሲካ በዕብራይስጥ"ፓሳሕ" ማለት ሲሆን ትርጓሜውም "አለፈ" "ተሻገረ" ማለት ነው። የእስራኤል ልጆች በግብጽ አገር በግ አርደው ደሙን በደጃቸው በመርጨት ከእግዚአብሔር ቁጣ ዳኑ። የእግዚአብሔር መልአክ በዚያች ሌሊት ግብጻውያንን ሲቀሥፍ ደም በነበረበት ቤት አልፎ ስላልገደለ ወይም ደም የተረጨበትን ቤት ስላለፈ ቀኑ ፋሲካ ተባለ። ለፋሲካ የሚታረደውም በግ ፋሲካ ይባላል (ዘጸ 12፡1-13)። በየዓመቱ በግ እያረዱ የእስራኤል ልጆች በመጀመሪያ ወራቸው በ14ኛው ቀን የፋሲካን በዓል ያከብራሉ። ከዚያም ምሽት እስከ አንድ ሳምንት ድረስ የቦካውን ነገር ለመብላት ስላልተፈቀደላቸው የሙሉ ሳምንት በዓል "የቂጣ በዓል" ተባለ። የቂጣ እንጀራ መብላት የእስራኤል ልጆች በችኮላ ከግብጽ መውጣታቸውን የሚያስታውስ የመታሰቢያ ምልክት ነው(ዘጸ 12፡18-20፤ ዘዳ 16፡1-3)።

እግዚአብሔርም እንዲህ በማለት ትእዛዝ ሰጣቸው፡-"ለጉዞ እንደተዘጋጀ ሰው ሆናችሁ ልብሳችሁን በአጭር በመታጠቅ ጫማችሁን አድርጋችሁ፣ በትራችሁን በእጃችሁ ይዛችሁ በችኮላ(የበግ ወይም የፍየል ጥቦት) ብሉት፤ እርሱም እኔን እግዚአብሔርን የምታከብሩበት የፋሲካ በዓል ይሁንላችሁ" (ዘጸ 11፡11)።

- **የመጀመሪያው ፋሲካ እንዴትና የት ተከበረ (ተደረገ)?**

የመጀመሪያው ፋሲካ እዛው ግብጽ ውስጥ በችኮላ ተከበረ(ዘጸ12፡1-20)፤ ነገር ግን ትክክለኛው ፋሲካ ወይም "ማለፍ" ወይም "መሻገር" የሚለውን ትርጉም በሚያሳይ መልኩ የተከበረው የግብጽን የባርነት ኑሮ አልፈው ከወጡ በኋላ ነው(ዘጸ. 12. 43-51)። ሙሴ በእስራኤል ሕዝብ አለቆች ሁሉ ጠርቶ እንዲህ አላቸው "ቤተሰባችሁ ሁሉ የፋሲካን በዓል እንዲያከብር ከእናንተ እያንዳንዱ የበግ ወይም የፍየል ጥቦት መርጦ ይረድ፤ ጭብጥ የሚሞላ የሂሶጵ ቅጠል ውሰዱ፤ በሳሕን ያለውንም ደም በቅጠሉ እየነከራችሁ የቤታችሁን በር መቃኖችና በላይ በኩል ያለውን ጉበን ቀቡ፤ እስከ ማግሥቱ ጠዋት ድረስ ማንም ሰው ከቤቱ አይውጣ። እግዚአብሔር ግብጻውያንን በሞት ለመቅጣት በግብጽ ምድር ያልፋል፤ በጉበንና በመቃኖች ላይ ያለውንም ደም በሚያይበት ጊዜ አልፎ ይሄዳል፤ የሞት መልአክም ወደየቤታችሁ ገብቶ እናንተን እንዳይገድል ያደርጋል፤ እናንተና ልጆቻችሁ ይህን ሥርዓት ለዘለዓለም

ትጠብቁታላችሁ፤ እግዚአብሔር ሊያወርሳችሁ ተስፋ ወደ ሰጣችሁ ምድር ስትገቡም ይህን ሥርዓት ትፈጽማላችሁ"(ዘጸ 11፡21-25)።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ሳምንት የፋሲካ ሳምንት ነበረ(ሉቃ 22፡14-16፤ ዮሐ 18፡38-40)። እርሱም ንጹሕ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ደሙን ስላፈሰሰልን "ፋሲካችን ክርስቶስ" ተባለ(1ቆሮ 5፡7፤ 1ጴጥ 1፡18-19)። ስለዚህ የክርስቶስ ትንሣኤ በዓል ፋሲካ ተብሎ ይጠራል።

- ***የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን እስራኤላውያንን አለቅም በማለቱ እልከኛ በሆነ ጊዜ መቅሠፍት እንደመጣባቸው ተደጋግሞ ተገልጿል፤ ለመሆኑ መቅሠፍት ማለት ምን ማለት ነው? የመቅሠፍት ዋና ምክንያትስ ምንድን ነው?***

መቅሠፍት ማለት በኃጢአት ምክንያት በሰው ላይ የሚመጣው ችግርና በሽታ ነው(ዘፍ 12፡17፤ ዘኁ 16፡46፤ 1ነገ 8፡37-40፤ ራእ 9፡20)። ከብሉይ ኪዳን እንደምንረዳው ከሆነ የመቅሠፍት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚባሉት አለመታዘዝ፣ እልከኛነት፣ ዐመፅ፣ ትእዛዛትን መተላለፍ፣ ጣዖትን ማምለክ፣ በሥጋ ፈቃድ መኖር በአጠቃላይ እግዚአብሔርና ትእዛዛቱን ረስቶ መኖር ናቸው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ይባርካል እንጂ በመቅሠፍት የሚደሰት አምላክ አይደለም፤ ነገር ግን ሕዝቡ ከእልከኝነታቸው እንዲመለሱ፣ ንስሓ እንዲገቡና ትእዛዛቱን ጠብቀው በበረከት እንዲኖሩ ያስተምራቸዋል። ለምሳሌ ግብጻውያን እልከኞች በመሆናቸው እግዚአብሔር በዐሥር መቅሠፍቶች መታቸው። እነርሱም የውሃ ወደ ደም መለወጥ፣ ጓጉንቸር፣ ቅማል፣ የዝንብ መንጋዎች፣ ቸነፈር፣ ቁስል፣ ነጎድጓድና በረዶ፣ አንበጣዎች፣ ጨለማና የበኩር ልጅ ሞት ናቸው(ዘጸ 7-12)።

- ***ከእስራኤላውያን የግብጽ የባርነት ኑሮ አልፎ ወደ ተስፋይቱ ምድር ካደረጉት ጉዞ በተያያዘ መልኩ "መና" ስለተባለው ምግብ ይነገራል። ለመሆኑ መና ማለት ምን ማለት ነው?***

በዕብራይስጥ ቋንቋ መና ማለት "ይህ ምንድን ነው?" ማለት ነው(ዘጸ 16፡15)። እስራኤላውያን በተራቡ ጊዜ በምሽት ብዙ ድርጭቶች እየበረሩ መጥተው ሰፈሩን ሸፈኑት። በማለዳ ደግሞ በሰፈሩ ዙሪያ ጤዛ ነበር፤ ጤዛውም ከተነነ በኋላ ደቃቃና ስስ የሆነ ነገር በበረሓማው ምድር ላይ ታየ፤ እርሱም በምድር ላይ ያረፈ ዐመዳይ ይመስል ነበር። እስራኤላውያን ባዩት ጊዜ ምን እንደሆነ ባለማወቃቸው "ይህ ነገር ምንድን ነው?" በማለት እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ(ዘጸ 16፡13-16)። ከዚህ በመነሣት ነው "መና" የሚለው ስም የተገኘው። ስለዚህ መና ማለት "ይህ ነገር ምንድን ነው" ማለት ነው።

ጠዋት ጠዋት ጠል ካለፈ በኋላ እንደ ደቃቅ ውርጭ ያለ በምድር ላይ ይታይ ነበር፤ የእስራኤል ሕዝብም ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ ተመገቡት(ዘጸ 16፡35)። እስራኤላውያን ጠዋት ጠዋት ያንን እየለቀሙ ይመገቡ ነበር። ለማሳደር በሞከሩ ጊዜ ተበላሸ፤ ተላ። በስድስተኛው ቀን ግን የተረፈው መና አልተበላሸምና ለሰባተኛው ቀን ምግብ ሆነ። ለተተኪው ትውልድ ምስክር እንዲሆን አሮን ከመናው በጎመር ውስጥ ከትቶ በቅድስተ ቅዱሳን አኖረው(ዘጸ16፡13-36፤ ዕብ 9፡4)። ከ40 ዓመት በኋላ እስራኤል በኢያሪኮ ምሥራቅ በጌልጌላ ሰፍረው ሳሉ ሌላ ምግብ ስላገኙ መናው ቀረ(ኢያ 50፡10-12)። እግዚአብሔር መናን ሲሰጥ እንዴት ወይም ምን እንደሆነ አይታወቅም። እግዚአብሔር መናን በመስጠቱ ሰው በዚህ ብቻ እንደማይኖር በእግዚአብሔር ቃልም እንደሚኖር(ዘዳ 8፡3-16)፤ ሰባተኛው ቀን እንዲያከብር አስተማረ(ዘጸ 16፡19-30፤ 20፡8-10)። ክርስቶስ የእስራኤል መና ከጠቀሰ በኋላ የሥጋው ሕይወትነት ከዚያ ይልቅ እጅግ የበለጠ መሆኑን አሳየ(ዮሐ 6፡26-71)።

- ***ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ማውጣት ጋር በተያያዘ መልኩ የአሮን ስም ሲጠራ ይሰማል፤ ለመሆኑ አሮን ማን ነው?***

አሮን የሙሴና የማርያም ወንድም ነው(ዘኍ 26፡59፤ ዘጸ 6፡20)። ስሙ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው እግዚአብሔር ራሱን ለሙሴ በገለጠበት ጊዜ ነው፤ በዚያን ጊዜ ሙሴ የእስራኤል መሪ እንዲሆን መርጦት ነበር፤ ነገር ግን ሙሴ "አፌ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ" በማለት ለመታዘዝ አለመውደዱን በገለጠ ጊዜ እግዚአብሔር "ወንድምህ አሮን አፍ ይሆንልሃል" ብሎ መለሰለት(ዘጸ 4፡14-16)።

የይሁዳ ነገድ አለቃ እኅት የሆነችውን ኤልሳቤጥ የተባለችውን ሴት አግብቶ ከእርስዋ ናዳብ፣ አብድዩ፣ አልዓዛርና ኢታምር የተባሉ አራት ልጆችን ወለደ(ዘጸ 6፡23)። ሙሴ ወደ ፈርዖን በቀረበ ቁጥር ከዚያም በኋላ የአርባው ዓመት የምድረ በዳ ጉዞ እስኪያልፍ ድረስ ሙሴ በሚሠራው ሥራ ሁሉ አሮን የቅርብ ረዳቱ ነበረ። የእስራኤል ልጆች ከአማሌቅ ጋር በተዋጉ ጊዜ አሮንና ሖር የሙሴን እጆች ይደግፉ ነበር(ዘጸ 17፡9-12)። ሆኖም የእስራኤል ልጆች ይሰግዱለት ዘንድ የወርቅ ጥጃን በመሥራቱ እግዚአብሔርን ሳያስቆጣው አልቀረም(ዘጸ 32)። አሮን ለተለየ አገልግሎት በእግዚአብሔር ተመረጠ(ዘኍ 17)። ቢሆንም መሪባ በተባለው ስፍራ ከሙሴ ጋር ሆኖ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለማክበሩ ኃጢአት ሠራ(ዘኍ 20፡12)።

- **አሮን ከክህነት ሕይወት ጋር ለምን ተያይዞ ይጠቀሳል? ክህነት ማለት ምን ማለት ነው?**

አሮን ሊቀ ካህናት እንዲሆን በመመረጡ ከሌዊ ወገን ካህናት የመጀመሪያው ሆነ(ዘጸ 28፡1)። ልጆቹም ካህናት እንዲሆኑ ተቀደሱ(ዘሌ 8፡12-13፣ 30)። በ123 ዓመቱ ሲሞት ሊቀ ካህንነቱ ለልጁ ለአልዓዛር ተሰጠ(ዘኍ 20፡22-29፤ 33፡38፤ ዘዳ 10፡6)። ከዚህም በላይ በአዲስ ኪዳን አሮን የክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ተቆጥሮአል(ዕብ 5፡4-5)።

ክህነት (ካህን) በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሆኖ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ ነው። ካህን ማለት አገልጋይ እንደማለት ነው። ከብሉይ ኪዳን አኳያ ስናይ አገልግሎቱ መሥዋዕትን በመሠዋትና ጸሎት በመጸለይ ይፈጸማል። ካህን በማንኛውም ሃይማኖት አለ(ዘፍ 41፡45፤ 1ሳሙ 6፡2፤ ሐዋ 14፡13)። በመጀመሪያ እንደ አቤልና ቃየል ሰው ለራሱ የራሱን መሥዋዕት አቅራቢና ሠዊ ነበር(ዘፍ 4፡3-4)። በኋላም እንደ ኖኅና እንደ አብርሃም አባት ለቤተሰቡ ይሠዋ ነበር(ዘፍ 8፡20፤ 12፤ 7፡13-18)። ሕግ ሲሰጥ ግን አሮንና ልጆቹ ለእስራኤል ካህናት እንዲሆኑ ተመረጡ(ዘጸ 28፡1)። ከአሮን ቤተሰብ ውጭ የሌዊ ዘሮች በመቅደስ ያገለግሉ ነበር እንጂ መሥዋዕትን አልሠውም(ዘኍ 3፡5-10)።

ሆኖም ከአሮን ልጆች ያልሆነ ሌላ ሰው ቢሆንም እግዚአብሔር ራሱን ከገለጠለት እንደ ጌዴዎን መሥዋዕት ይሠዋ ነበር(መሳፍ 6፡18-26፤ 13፡16)፤ እንደዚሁም የእግዚአብሔር ካህናት ሲጠፉ ኤልያስ መሥዋዕት ሠዋ(1ነገ 18፡30)። ከአሮን ልጆችም ነውር ያለበት ከተገኘ አይሾምም ነበር(ዘሌ 21፡16-24)።

አሮንና ልጆቹ ሲሾሙ ልዩ ልብስ ለብሰው በዘይት ይቀቡ ነበር(ዘጸ 28፡40፤ ዘሌ 8)። አገልግሎታቸውንም በብዙ ጥንቃቄ እንዲፈጽሙ ታዘዙ(ዘጸ 30፡17-21)። በዚያን ጊዜ የካህናት ሥራ በመቅደስ ማገልገል(ዘኍ 16፡40፤ 18፡5)፤ ሕግን ለሕዝብ ማስተማር(2ዜና መ. 15፡3፤ ሕዝ 7፡26)፤ በኡሪምና ቱሚም የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ(ዘጸ 28፡30፤ ዕዝ 2፡63)፤ ተላላፊ በሽታ ያለባቸውን መለየት ነበር(ዘሌ 13፡1-3)።

በአጠቃላይ ካህናት በቤተ መቅደስ የሚፈጽሙትን አገልግሎት በሦስት (3) ይከፈላል፡-

1) ***ዕለታዊ አገልግሎት፡-*** ይህ ጠዋትና ማታ የሚቃጠል መሥዋዕትን የመሠዋት፣ በቅድስት መብራቶችን የማብራት፣ ዕጣን የማጠን፣ ሰው የሚያመጣውን መሥዋዕትም የማቅረብ አገልግሎት ነው(ዘጸ 29፡38-39፤ 30፡1-8)።

2) **ሳምንታዊ አገልግሎት፡-** በየሰንበቱ ዐሥራ ሁለት የመገኝቱን ኅብስት በገበታው ላይ የማኖር አገልግሎት ነው(ዘሌ 24፡5-9)፡፡
3) **ዓመታዊ አገልግሎት፡-** በማስተሥረያ ቀን ልዩ ሥርዓትን የመፈጸም አገልግሎት ነው(ዘሌ 16)፡፡

### ➢ ሊቀ ካህናት አመጣጡ ከየት ነው? የአገልግሎት ተግባሩስ ምንድን ነው?

ሊቀ ካህናት ማለት ካህናትን የሚቆጣጠር የካህናት አለቃ ማለት ነው፡፡ ይህ ማዕረግ በመጀመሪያ ለአሮን በኋላም ከአሮን ቤተሰብ ለዋናው ስለተሰጠ ከአሮን ጋር በተያያዘ መልኩ ብዙ ጊዜ ሲጠቀስ ይሰማል፡፡ በመጀመሪያ ጊዜ አልቅናው እስከ ሞት ድረስ ነበር፤ በኋላ ግን ነገሥታት እንደፈለጉ ሊቃነ ካህናትን ይሾሙና ይሽሩ ነበር፡፡ በክርስቶስ ጊዜም እንደነ ሐና ያሉ በሮም መንግሥት የተሾሙ ሊቃነ ካህናት ነበሩ(1ነገ 2፡26፤ ሉቃ 3፡፫2)፡፡ የሊቃነ ካህናቱ ልብሶች በዕውቀት(በልዩ ዓይነት) የተሠሩ ነበሩ፡፡ እነርሱም ኡሪምና ቱሚም የተቀመጡበት የደረት ኪስ፣ ኤፉድ፣ ቀሚስ፣ ዥንጉርጉር ሸሚዝ፣ መጠምጠሚያ "ቅድስና ለእግዚአብሔር" የሚል የተቀረጸበት የወርቅ አክሊልና መታጠቂያ ናቸው(ዘጸ 28፡1-39)፡፡

አሮን ሲሾም ሙሴ እንዲያለብሰው በዘይትም እንዲቀባው ታዘዘ(ዘጸ 29፡1-9)፡፡ ሊቀ ካህናት ቤተ መቅደስን ያስተዳድራል፣ ካህናትንም ይቆጣጠራል(1ሳሙ 3፡12-13፤ 2ነገ 12፡7፤ 22፡4)፡፡ በሸንጎም ላይ ሊቀ መንበር ይሆን ነበር(ማቴ 26፡57-65)፡፡ ሊቀ ካህናት በማሥተሰረያ ቀን ልዩ መሥዋዕት ለሕዝብ ያቀርባል፤ በዚያን ቀን ብቻ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቶ በታቦቱ ላይ ደም ይረጫል(ዘሌ 16)፡፡

### ➢ ኡሪምና ቱሚም ምንድን ናቸው? ከሊቀ ካህናቱ ጋር ምን ግንኙነት አላቸው?

ኡሪምና ቱሚም ሊቀ ካህናት በሚለብሰው በኤፉዱ ላይ ባለው የደረት ኪስ ውስጥ የሚከቱት ሁለት ዕቃዎች ናቸው(ዘጸ 28፡30፤ ዘዳ 33፡8)፡፡ ኡሪምና ቱሚም ከምን እንደተሠሩ ወይም እንዴት ያሉ እንደነበሩ አልተገለጠም፤ በኡሪምና በቱሚም ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ይጠየቅ እንደነበረ ተገልጿል (ዘኍ 27፡21፤ ዕዝ 2፡63)፡፡ ዳዊት በኡሪም(በኤፉድ) እግዚአብሔርን በጠየቀ ጊዜ መልስ አገኘ(1ሳሙ 23፡6-12)፡፡ ሳኦል ግን ቢጠይቅ መልስ አጣ(1ሳሙ28፡6)፡፡

### ➢ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ከአሮን ክህነት ይበልጣል ወይስ ያንሳል?

መልከ ጸዴቅ ማለት የጽድቅ ንጉሥ ማለት ነው፡፡ የሳሌም ንጉሥ ነበር፡፡ ይህም የሰላም ንጉሥ ማለት ነው፡፡ ምናልባትም "ሳሌም ኢየሩሳሌም ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔርም ካህን ነበር(ዕብ 7፡1-3)፡፡ አብርሃም ከጦርነት በተመለሰ ጊዜ መልከ ጼዴቅ ባረከው፤ አብርሃምም ከሀብቱ ሁሉ ዐሥራትን ሰጠው (ዘፍ 14፡18-20)፡፡ክህነቱ በእርግጥም ከአሮን ክህነት እንደሚበልጥ ተጽፎለታል፡፡ ይህም አንደኛ በሥጋዊ ትውልድ ሳይሆን በእግዚአብሔር መሐላ በመሾሙ(ዕብ 5፡5-6፤ 7፡13-17)፡፡ ሁለተኛ በሞት ሳይወሰን ለዘለዓለም በማገልገሉ ነው(ዕብ 6፡20፤7፡3 እና ከ23-25)፡፡ ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ በእግዚአብሔር ሊቀ ካህናት በመባሉ የአሮንን ክህነት አስቀርቶአል(ዕብ 5፡7-10፤ 7፡11-19)፡፡

### ➢ የክርስቶስ ክህነት ከመልከ ጼዴቅና ከአሮን ክህነት ጋር እንዴት ሊገለጽ ይችላል?

ክርስቶስ እንደ መልከ ጼዴቅ ካህን ሆኖ ለኃጢአት ሁሉ የሚበቃውን መሥዋዕት አቅርቦአልና የአሮን ክህነት አስቀርቶአል(ዕብ 7፡11-28)፡፡ የክህነቱን ሥራ የፈጸመው በምድራዊ መቅደስ ሳይሆን በሰማያዊ መቅደስ፣ በእንስሳት ደም ሳይሆን በራሱ ደም ነው(ዕብ 9፡11-12)፡፡ አሁን ለኃጢአት ሌላ የደም መሥዋዕት ማቅረብ አያስፈልግም፤ ሆኖም ምእመናን ሁሉ በክርስቶስ ሥራ መሠረት መንፈሳዊ መሥዋዕትን ለእግዚአብሔር ስለሚያቀርቡ የሚሰጡትን ምስክርነትም ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ስለሚያደርሱ ካህናት ተብለዋል(ሮሜ 12፡1፣ ዕብ 10፡19-25፤ 1ጴጥ 2፡5-9፤ ራእ 1፡5-6)፡፡

ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት በመሆን ራሱን አንድ ጊዜ ሠውቶ ወደ ሰማያዊ መቅደስ ገብቶአልና የሊቀ ካህናት ሥራ በአዲስ ኪዳን ቀርቶአል(ዕብ 9፡1-28፤ 10፡12-21)።

- **በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናትና መሥዋዕት በተያያዘ መልኩ ሲገልጹ ይሰማል፤ ለመሆኑ መሥዋዕት ማለት ምን ማለት ነው? አደራረጉስ በምን ዓይነት መልኩ ይከናወን ነበር?**

እንደ ብሉይ ኪዳን አገላለጽ(የኦሪት መጻሕፍት) ሰው ለአምላኩ አንዳች ነገር ቢሰጥ ወይም ቢያቃጥል ያ ነገር መሥዋዕት ወይም ቁርባን ይባላል። መሥዋዕቱም እንደ ሥርዓቱ ዓይነት ሲሠዋ መሠዋቱ ልዩ ልዩ አሳብ ሊገለጥ ይችላል። ለምሳሌ በአምላክ ፊት ተቀባይነትን ለማግኘት ወይም ለማጠንከር ይሆናል፤ እንዲሁም የሰጪውም እምነት ወይም ንስሓ ምስጋና ወይም ፍቅር ያሳያል። መሥዋዕትን ያቀርቡ የነበሩ ሰዎች አንድ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ እስራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ አረማውያንም ደግሞ ለጣዖቶቻቸው ያቀርቡ ነበር።

በብሉይ ኪዳን ቃሉ ለመጀመሪያ ጊዜ በዘፍ 4፡4 ላይ ይገኛል። እንዲሁም መሠረተ አሳቡ በዘፍ 3፡21 ላይ ተገልጾአል። ከሙሴ በፊት የጥንት አባቶች ለእግዚአብሔር ይሠው ነበር(ዘፍ 4፤ 8፡20፤ 12፡7)። በኦሪት ሕግ ግን የካህናት ወገኖች ብቻ እንዲሠው ተፈቅዶላቸዋል(ዘኁ 3፡10)። የኦሪትም መሥዋዕት ከሥጋ ከእህልና ከመጠጥ ነበሩ። ከሥጋም ሲሆን ነውር ከሌላቸው ንጹሓን ከተባሉ እንስሶችና ወፎች መሆን ነበረበት(ዘፍ 8፡20ዘሌ 22፡17-25)።እግዚአብሔር ከእስራኤል ያዘዛቸው መሥዋዕቶች አምስት ዓይነት ናቸው። እነዚህም የሚቃጠል መሥዋዕት፣ የእህል ቁርባን፣ የደኅንነት መሥዋዕት፣ የኃጢአት መሥዋዕትና የበደል መሥዋዕት ናቸው(ዘሌ1-5)።

የመሥዋዕት አቀራረብ ሥነ ሥርዓት በእንስሳት ሲፈጸም፡-

1) እንስሳው ንጹሕ የሆነና እንከን የሌለበት ነበር(ዘጸ 12፡5፤ ዘሌ 22፡24-25፤ 1ጴጥ 1፡18-19)።
2) አቅራቢው እጁን በእንስሳው ራስ ላይ ይጭናል(ዘሌ 1፡4)። ይህን በማድረጉ በምሳሌነት ራሱን ከእንስሳው ጋር አንድ ያደርጋል፤ ኃጢአቱንም ያሸክመዋል(ዘሌ 16፡21፤ ኢሳ 53፡6፤ 1ጴጥ 2፡24)።
3) አቅራቢው ያደርገዋል፤ የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና(ሮሜ 6፡23፤ ዕብ 9፡28)።
4) ካህን የመሥዋዕቱን ደም በእግዚአብሔር ፊት ያቀርባል(ዘሌ 1፡5፤ 17፡11፤ ዕብ 9፡12)።
5) ካህን ከእንስሳው እንደ መሥዋዕቱ ዓይነት ልዩ ልዩ ክፍልና ብልት ያቃጥላል። ይህ በምሳሌነት አቅራቢው ራሱን ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንደሚያቀርብ ይገልጣል(ዘፍ 8፡21፤ ሮሜ 12፡1፤ 2ቆሮ 2፡14-16፤ ኤፌ 5፡2)።
6) ካህን አንዳንድ ጊዜም አቅራቢው ከእንስሳ ያልተቃጠለውን በመሠዊያ አጠገብ ይበላል(ዘሌ 6፡26)፡፡ ይህም በመሥዋዕቱ መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዳለው ያሳየል(1ቆሮ 10፡14-22፤ የይሁዳ መልእክት ቁ. 12)።

**የትምህርቱ አዘጋጅ፡- አባ ምሥራቅ ጥዩ**
**የትምህርቱ አስተባባሪ፡- አቶ ተስፋዬ ባደገ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመለሱ በኋላ ወደ ሀገረስብከቱ የተልእኮ ትምህርት ዝግጅት ክፍል ይላኩት፡፡**

**የተማሪው/ዋ ስም -----------------------------------ኮድ-------- ቁምስና-------------------ውጤት---------**

1. *ዐሥራትን በተመለከተ ከሚከተሉት ውስጥ ትክክል ያልሆነውን ምረጥ፡፡ ሀ) እግዚአብሔር ምድር ከምታፈራውና ከከብትም ወገን ሁሉ ዐሥራት እንዲሰጥ አዘዘ ለ) እንደ ኦሪት ዘፍጥረት አገላለጽ ለመጀመሪያ ጊዜ ዐሥራት የከፈለው መልከ ጼዴቅ ነው ሐ) በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ገቢ ያለው እያንዳንዱ ግለ ሰው ዛሬም ቢሆን ዐሥራት የመክፈል ግዴታ አለበት መ) ዛሬም ቢሆን ዐሥራት የማይከፍል ገቢ ያለው ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔር ባለ እዳ ይሆናል ሠ) ሁሉም ትክክል ናቸው፡፡*
2. *የእስራኤላውያን የመጀመሪያው የፋሲካ በዓል አከባበር በተመለከተ ትክክል ያልሆነውን ምረጥ (ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በመጀመሪያ ዘጸ 12 በማስተዋል ደጋግሞ ማንበብ ያስፈልጋል)፡፡ ሀ) እስራኤላውያን እንዲያገለግሎአቸው ከሌላ ቦታ በግዢም ሆነ በሌላ መልኩ ከእነርሱ ጋር ይኖሩ የነበሩ ወንዶች አገልጋዮች(ባዕዳን የነበሩ) የፋሲካን በዓል ከእስራኤላውያን ጋር ማክበር እንዲችሉ ግዴታ መገረዝ ነበረባቸው፤ ለ) በታረደው የፋሲካ በግ ደም የቤታቸው መቃ እንዲቀቡ የታዘዙት የሞት መልአክ ወደየቤታቸው ገብቶ እንዳይገድላቸው የሚጠቅም የመለያ ምልክት እንዲሆን ነበር፤ ሐ) የፋሲካው በግ ሥጋ በዚያኑ ሌሊት እየጠበሱ ከመራር ቅጠልና ካልቦካ ቂጣ ጋር እንዲበሉት ታዘዙ፤ መ) እስራኤላውያን ግብጽ ውስጥ በባርነት አራት መቶ ስልሳ ዓመት ከኖሩ በኋላ ነው ግብጽን ለቀው የወጡት፤ ሠ) የአይሁድ የፋሲካ በዓል በሚከበርበትና ጠቦታቸው በሚታረድበት ሰዓት ክርስቶስ ደሙን አፍስሶ ዓለምን በማዳኑ ምክንያት ክርስቶስ የአዲስ ኪዳን የፋሲካ በግ ተባለ፡፡*
3. *እስራኤላውያን በምድረ በዳ ጉዞአቸው ውስጥ እያሉ በረሃብ ልናልቅ ነው ብላው ሲጮኹ መና ተጠማን ብለው ሲጮኹ ደግሞ ውሃ አዘነመላቸው፡፡ ከሚከተሉት ውስጥ ከሰማይ ስለወረደው መና እና ከአለት ስለፈለቀው ውሃ ትክክለኛ ያልሆነው የትኛውን ነው? (ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ዘጸ ምዕራፍ 16 እና 17 ደጋግሞ ማንበብ ያስፈልጋል) ሀ) ሙሴ ለእስራኤላውያን ለሰባት ቀን በተከታታይ ከሰማይ የወረደውን መና ለምግብነት ይውል ዘንድ እንዲሰበስቡ አዘዛቸው፤ ለ) ሕዝቡ ውሃ በተጠሙ ጊዜ ሙሴን በድንጋይ የመውገር ያህል ተዘጋጅተው ነበር፤ ሐ) ሙሴ የአባይን ወንዝ የመታበትን በትር በመጠቀም በሲና ተራራ የነበረው አለት ሲመታው ሕዝቡ የሚጠጡት ውሃ ከውስጡ ፈለቀ፤ መ) መና በወረደ ጊዜ እያንዳንዱ ሰው ለዕለት ምግቡ የሚያስፈልገውን ብቻ እንዲሰበስብ ተፈቀደለት፤ ሠ) ሁሉም ልክ ናቸው፡፡*
4. *እንደ ኦሪት መጻሕፍት ስለ አሮን ወገኖችና ስለ ካህናት ዋና ዋና ተግባራት ከሚባሉት ውስጥ የማይመደበው የትኛውን ነው? ሀ) መቅደስ ላይ ሆኖ የራሱንና የሕዝቡን መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ፤ ለ) ሕግን ማስተማር፤ ሐ) ዕለታዊ፣ ሳምንታዊና ዓመታዊ አገልግሎቶችን ማከናወን፤ መ) አሮንና ልጆቹ ለእስራኤል ካህናት እንዲሆኑ ተመረጡ፤ ነገር ግን የሌዊ ዘሮች በመቅደሱ እንዲያገለግሉ ተፈቀደላቸው፤ ሠ) ካህናት የሕዝቡን ንስሓ ይሰሙ ነበር(ንስሓ ያስገቡ ነበር)፡፡*
5. *በሙሴ አማካይነት እግዚአብሔር ለሕዝቡ ውሃ ያፈለቀበት የሲና ተራራ አለት ስሙ ከዚህ ታላቅ ተአምራዊ ክንውን በኋላ የቦታው ስም ምን ተብሎ ተጠራ? በዚህ ስም የተጠራበት ምክንያቱስ ምንድን ነው (ወይም የቦታው ስም ትርጓሜ ምንድን ነው?) ምላሹ ከጀርባ ይጻፉ፡፡*
6. *በዘጸ 32፡32-35 ላይ ሙሴ ለእግዚአብሔር እንዲህ አለው "እባክህን ኀጢአታቸውን ይቅር በል፤ ይቅር የማትላቸው ከሆነ ግን የሕዝብህ ስሞች ከተጻፉበት መዝገብ የእኔን ስም ደምስስ፡፡" እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መለሰለት "ስሞቻቸውን ከመዝገቤ የምደመስሰው ኃጢአት በመሥራታቸው ያሳዘኑኝን ሰዎች ነው" አለው፡፡ ለመሆኑ ይህ "የሕዝቦች ስሞች የተጻፉበት መዝገብ" ወይም "የእግዚአብሔር መዝገብ" የተባለው ምንድን ነው? ወይም ምንን ያመለክታል?*